# ጦርነትና ግጭት ያረበበበት ምርጫ ምን ያተርፍልናል?

### የፖለቲካ ፓርቲዎች ፕሮግራም ንጽጽራዊ ዳሰሳ

ዋዜማ ራዲዮ

ሰኔ 2013 ዓ. ም

## አሕጽሮተ ቃላት

ኢሕአዴግ- የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር

ኢዜማ- የኢትዮጵያዊያን ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ

ነኢፓ- ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ

አብን- የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ

## ጦርነትና ግጭት ያረበበበት ምርጫ ምን ያተርፍልናል?

በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም የሚካሄደው ጠቅላላ ምርጫ የሀገሪቱን የዴሞክራሲ ልምምድ አንድም ወደተሻለ አልያም ወደባሰ ምስቅልቅል ሊወስደው ይችል ይሆናል፡፡ ምርጫው የሚካሄደው በትግራይ ክልል ደም አፋሳሽ ጦርነት እየተካሄደ፣ በቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ብሄር ተኮር ግጭት፣ መፈናቀልና ውጥረት ያለመረጋጋት ስሜቱን አንሮት ባለበት ወቅት ነው፡፡ የኮሮና ወረርሽኝም በምርጫው ሂደት ላይ እንዲሁም በዕለታዊ ኑሯችን ላይ ያስከተለውና እያስከተለ ያለው ጫና በዋዛ የሚታለፍ አይደለም፡፡

መሠረታቸውን በኦሮሚያ ክልል ያደረጉት የኦሮሞ ነጻነት ግንባር እና የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግሬስ ፓርቲዎች የቅድመ-ምርጫው ሂደት ነጻና ፍትሃዊ አይደለም በማለት ከወዲሁ ከክልላዊው እና ከሕዝብ ተወካዮች ምርጫ ከወዲሁ ራሳቸውን አግልለዋል፡፡ የምርጫው ድባብ የጦርነትና የስብዓዊ ቀውስ ያረበቡበት ቢሆንም፣ ከሦስት ዓመት በፊት በገዥው ኢሕአዴግ ውስጥ በተፈጠረው ቀውስና በሕዝብ አመጽ ወደ ሥልጣን ለመጡት ጠቅላይ ሚንስትር አቢይ አሕመድ ቅቡልነት ወይም ቢያንስ ሕጋዊ መሠረት ያለው መንግሥት ለመሆን ምርጫው ቁልፍ ርምጃ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ የሀገሪቱን መጻዒ ዕድል በመወሰን በኩልም ምርጫው መካሄዱ ጉልህ አንድምታ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡

ዋዜማ ራዲዮ በዚህ ውጥንቅጥ የፖለቲካ ድባብ ውስጥ የሚደረገው ጠቅላላ ምርጫ የትኞቹን ቁልፍ የሕዝብ አጀንዳዎች አንስቷል? በተለይ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሽኩቻ ዋና ማጠንጠኛ የሆኑት የብሄር ፌደራላዊ አወቃቀር ጉዳይ፣ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ፣ የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ እና በአዲስ አበባ ከተማ ባለቤትነትና አስተዳደር ጥያቄዎች ላይ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምን አቋም አላቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች በንጽጽር ተመልክታለች፡፡ ሀገሪቱ ብዙ ተግዳሮቶች ተጋርጠውባት ባለበት በዚህ ወቅት፣ ዋዜማ ሬዲዮ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የፖለቲካ ፕሮግራሞችና ርዕዮተ ዓለማዊ መስመሮች ምን እንደሆኑ በዚህ ሪፖርት በአንድ ላይ ተጨምቀው መቅረባቸው በታሪክ ተመዝግበው እንዲቀመጡ ለማድረግ ይረዳል የሚል እምነት አላት፡፡

ይህ ሪፖርት በማናቸውም መንገድ በምርጫው ሂደትም ሆነ ውጤት ላይ ፍርድ ለመስጠት ያለመ አይደለም፡፡ የሪፖርቱ ዐላማም አይደለም፡፡

ዋዜማ ራዲዮ ገለልተኛ የሚዲያ ተቋም ነው፡፡ በኢሜይል አድራሻ wazemaradio@gmail.com እንገኛለን፡፡

መልካም ንባብ

**መግቢያ**

ኢትዮጵያ በተለያዩ ምክንያቶች ሲራዘም የቆየውን ስድስተኛውን ሀገር ዐቀፍ ጠቅላላ ምርጫ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ታካሂዳለች፡፡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤቶች በሚደረገው በዚሁ ጠቅላላ ምርጫ የሚፎካከሩ የፓለቲካ ፓርቲዎችም የፖለቲካ ፕሮግራም እና የምርጫ ማንፌስቶ ቀርጸው ለሕዝብ ሲያስተዋውቁ ቆይተዋል፡፡ የፓርቲዎቹ የፓለቲካ ፕሮግራሞችም ሆኑ የምርጫ ማንፌስቶዎች በዋናነት ፖርቲዎቹ የሚከተሏቸውን የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና የውጭ ጉዳይ መርሆዎች እና ፖሊሲዎች የያዙ ሰነዶች ናቸው፡፡ ባጠቃላይ ፓርቲዎቹ ምርጫ አሸንፈው መንግሥት ቢመሠርቱ፣ መሬት ላይ የሚተገብሯቸውን መሠረታዊ አማራጭ ሃሳቦች በእነዚህ ሰነዶች ዘርዝረዋል ማለት ይቻላል፡፡

የፓርቲዎቹን ፕሮግራሞች መነሻ በማድረግ ዋዜማ ሬዲዮ የተወሰኑ ፓርቲዎች በተወሰኑ ቁልፍ ነጥቦች ላይ ባሏቸው አቋሞች ላይ መጠነኛ ንጽጽራዊ ዳሰሳ አድርጋለች፡፡ ይህ መለስተኛ ሪፖርት የዚሁ ንጽጽራዊ ዳሰሳ ውጤት ነው፡፡

**ለንጽጽሩ የተመረጡ ፓርቲዎች፤**

ዋዜማ ለንጽጽር የመረጠቻቸው ፓርቲዎች አምስት ሲሆኑ፣ እነሱም

1፤ ብልጽግና ፓርቲ (ገዥው ፓርቲ)፣

2፤ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ)፣

3፤ ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ)፣

4፤ እናት ፓርቲ እና

5፤ የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (አብን) ናቸው፡፡

አምስቱ ፓርቲዎች ለዚህ ንጽጽራዊ ሪፖርት የተመረጡት ለጠቅላላ ምርጫው ያቀረቧቸውን ዕጩዎች ብዛት እና ሀገር ዐቀፍ ፓርቲ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ከተመረጡት ፓርቲዎች ውስጥ ከአብን በስተቀር ሁሉም ሕብረ ብሄራዊ ወይም አገር አቀፍ ፓርቲዎች ሲሆኑ፣ ሁሉም ባለፉት ጥቂት ዐመታት የፖለቲካ ምኅዳሩን የተቀላቀሉ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ በተለይ ብልጽግና ፓርቲ ግን የቀድሞው ገዥ ፓርቲ ኢሕአዴግ ወራሽ በመሆኑ፣ የነባርነትን እና አዲስነትን ገጽታዎች አጣምሮ የያዘ ፓርቲ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**ማነጻጸሪያ መስፈርቶች፤** ለንጽጽራዊ ዳሰሳው የተመረጡት ፓርቲዎች በፖለቲካ ፕሮግራማቸው የሚያራምዱትን የፖለቲካ አቋም እና ርዕዮተ ዐለም ለማነጻጸር ዋዜማ አምስት ነጥቦችን መርጣለች፡፡ እነሱም፣

1፤ ብሄር ፌደራሊዝም

2፤ የኢኮኖሚ ፖሊሲ

3፤ የውጭ ፖሊሲ

4፤ ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ እና

5፤ የአዲስ አበባ ከተማ ባለቤትነት ጥያቄ እና አስተዳደራዊ ዕጣ ፋንታ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት አምስት ማነጻጸሪያ ነጥቦች የተመረጡት፣ በቀጣዩ ጠቅላላ ምርጫ መራጩ ሕዝብ ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች መካከል ጥቂቶቹ እንደሆኑ በማመን ነው፡፡ ፓርቲዎች በተጠቀሱት አምስት ጉዳዮች ዙሪያ በተለያየ መጠን አንድነትም ልዩነትም አላቸው፡፡

***የመረጃ ምንጭ፤*** አምስቱ ፓርቲዎች ለንጽጽር በተመረጡት ጉዳዮች ላይ ምን አቋም እንዳላቸው ለመረዳት፣ ሪፖርቱ የፓርቲዎቹን የፖለቲካ ፕሮግራሞች፣ የምርጫ ማንፌስቶዎች እና ኦፊሴላዊ የአቋም መግለጫዎች በምንጭነት ተጠቅሟል፡፡ የፓርቲዎቹ አመራሮች እና ወኪሎች በምርጫ ክርክሮች ላይ ያደረጓቸው ንግግሮች እና የሰጧቸው ማብራሪያዎችም እንዲሁ ለሪፖርቱ ግብዓት ሆነዋል፡፡

## I የብሄር ፌደራሊዝም

ብልጽግና ፓርቲ፣ ኢዜማ፣ አብን፣ አናት ፓርቲ እና ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ በፖለቲካ ፕሮግራማቸው ካሠፈሯቸው የፖለቲካ አቋሞች መካከል አንዱ ሀገረ መንግሥቱ ላለፉት 30 ዐመታት የተዋቀረበትን የብሄር ፌደራላዊ ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ ፓርቲዎቹ በቀጣዩ ጠቅላላ ምርጫ ቢያሸንፉ፣ አሁን ሥራ ላይ ያለውን ብሄር ተኮር ፌደራላዊ ሥርዓት ያስቀጥሉት፣ ያሻሽሉት ወይም ያስወግዱት እንደሆነ በፖለቲካ ፕሮግራማቸው ላይ አቋማቸውን አስፍረዋል፡፡ ሁሉም ፓርቲዎች የሀገረ መንግሥቱ አወቃቀር ያልተማከለ ወይም ፌደራላዊ መሆን እንዳለበት በጋራ የሚስማሙበት አንዱ መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ባላቸው ግዛቶች ወይም ክልሎች በመዋቀሯ ላይ ልዩነት የላቸውም፡፡ ልዩነታቸው ያለው ያልተማከለው ወይም ፌደራላዊ አወቃቀሩ ምን ዐይነት አወቃቀር ይሁን? እና ያልተማከለው ወይም ፌደራላዊው አወቃቀሩ በምን መስፈርት ላይ ተመስርቶ ይዋቀር? በሚለው ነጥብ ላይ ነው፡፡

ብሄር ተኮሩን የፌደራል አወቃቀር ከኢሕአዴግ የወረሰው ገዥው ብልጽግና ፓርቲ የብሄር፣ ሐይማኖት ወይም ሌላ ማንነቶችን በእኩል የሚያስተናግድ ኅብረ ብሄራዊ አንድነት መገንባት ዐላማው መሆኑን በፕሮግራሙ አስፍሯል፡፡ ፓርቲው ለሁሉም ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ዕውቅና የሚሰጥ እና መብታቸውን የሚያከብር እውነተኛ ኅብረ ብሄራዊ ፌደራላዊ ሥርዓት እገነባለሁ ይላል፡፡ እንደ ብልጽግና ፓርቲ ከሆነ፣ አሁን ያለው ፌደራላዊ አወቃቀር የአፈጻጸም ወይም ያተገባበር እንጂ በመርህ እና ርዕዮተ ዐለማዊ ፍልስፍና ደረጃ መሠረታዊ ችግር የለበትም፡፡ በፓርቲው እምነት የግለሰብ እና ቡድን መብቶች ሊበላለጡም ሆነ ሊነጣጠሉ አይገባም፤ ፓርቲውም ሁለቱን መብቶች አያበላልጥም ወይም ነጣጥሎ አይመለከትም፡፡ የብሄር ማንነት የሀገሪቱ ፖለቲካ ዋና ማጠንጠኛ መሆኑን የሚጠቅሰው ብልጽግና፣ የብሄር ማንነትን ከሀገራዊ ማንነት ጋር አጣጥሞ መጓዝ ዐላማው እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ ሀገሪቱ በቀደመ ታሪኳ የብሄር ጭቆናን አስተናግዳለች የሚል አቋምም አለው፡፡

ከሁሉም ፓርቲዎች በብሄር ፌደራላዊ አወቃቀር ላይ ስር ነቀል አቋም የያዘው የማኅበራዊ ፍትህ ርዕዮተ ዐለም አቀንቃኙ ኢዜማ ነው፡፡ የሀገሪቱ ችግሮች ሁሉ ምንጭ የብሄር ተኮሩ ሥርዓት አወቃቀር እንደሆነ የሚገልጸው ኢዜማ፣ ሥርዓቱ በተለያዩ የዘውጌ ማንነቶች መካከል መቃቃርን እና ግጭትን፣ አክራሪ ብሄርተኝነት እና የሃብት ሥርጭት ልዩነት እንደፈጠረ እና በዚህም ሥርዓቱ ራሱ በሀገሪቱ ብሄራዊ ደኅንነት ላይ አደጋ እንደደቀነ ያምናል፡፡ ፓርቲው ከዚህ እምነቱ በመነሳት በምርጫው የሕዝብ ይሁንታ አግኝቶ ሥልጣን ቢይዝ፣ በብሄር ወይም ቋንቋ ላይ የተመሠረተውን ፌደራላዊ አወቃቀር በመቀየር በምትኩ በዘር ወይም ዕምነት ላይ ያልተመሠረተ ያልተማከለ ወይም ፌደራላዊ ሥርዓት እንደሚተክል በፕሮግራሙ በማያሻማ ቋንቋ አስፍሯል፡፡ ፓርቲው እንደገና የሚያዋቅረው ያልተማከለ ወይም ፌደራላዊ ሥርዓት ደሞ፣ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን፣ የሕዝብ አሠፋፈር ለአስተዳደር እና ልማት ያለውን አመቺነት፣ ቋንቋን፣ ባህልን፣ ስነ ልቦናዊ ቁርኝትን፣ ታሪክን፣ የሃብት ስብጥርን፣ ፍትሃዊነትን እና ለብሄራዊ መግባባት ምቹ ሁኔታ መፍጠርን የመሳሰሉ መስፈርቶች ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ጥረት እንደሚያደርግ ገልጧል፡፡

የኢዜማ ገዥ ርዕዮተ ዐለም በዘውጌያዊ ወይም ብሄር ፖለቲካ ፋንታ የዜግነት ፖለቲካን ማራመድ ነው፡፡ በመሆኑም ፓርቲው ከፍተኛውን የሀገሪቱን ሕገ መንግሥታዊ ሉዓላዊ ሥልጣን አሁን የሥልጣኑ ባለቤት ከሆኑት ብሄሮች አንስቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ወይም በጠቅላላው ለሀገሪቱ ዜጎች ይሰጣል፡፡ ኢዜማ ከገዥው ብልጽግና ፓርቲ በተቃራኒ የቡድን መብቶች የሚመነጩት ከግለሰብ መብቶች ነው የሚል አቋም ነው ያለው፡፡

ሌላኛው ፓርቲ እናት ፓርቲ ደሞ እንደ ሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ ያልተማከለ አስተዳደር ወይም ፌደራላዊ ሥርዓት እንደሚያቀነቅን ይገልጽና፣ ከምንም በላይ ግን የሀገሪቱን አንድነት እንደሚያስቀድም በፖለቲካ ፕሮግራሙ ያሰፈረ ፓርቲ ነው፡፡ እናት ፓርቲ እንደ ኢዜማ ሁሉ አሁን ሥራ ላይ ያለው ፌደራላዊ ሥርዓት የግጭት መነሻ እንደሆነ ያምናል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግም ሀገረ መንግሥቱን እንደገና የማዋቀር ዕድል ቢያገኝ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን፣ የሕዝብ አሠፋፈርን፣ የልማት እና አስተዳደራዊ አመችነትን፣ ባህልን፣ ታሪክን፣ የሕዝብ ፍላጎትን እና ሌሎች ማኅበራዊ ትስስሮችን መሠረት ያደረገ እና የሕዝቡን ፍላጎት፣ ጥቅም እና አመለካከት ያካተተ አዲስ እና ሁለገብ ያልተማከለ አስተዳደር ወይም ፌደራላዊ ሥርዓት እንደሚያዋቅር አቋሙን ግልጽ አድርጓል፡፡ ከእነዚህ የሀገረ መንግሥት አወቃቀር መስፈርቶች በተጨማሪ ፓርቲው ጠቃሚ ሀገር በቀል የአስተዳደር ዘይቤዎችን ግምት ውስጥ አስገባለሁ በማለት ቃል ገብቷል፡፡ እናም ለሀገር በቀል የአስተዳደር ዘይቤዎች ትልቅ ትኩረት በመስጠት ረገድ፣ እናት ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች ይለያል ማለት ይቻላል፡፡ በፓርቲው እምነት የግለሰብ መብቶች ለሌሎች መብቶች ሁሉ ምሰሶ ናቸው፡፡

እናት ፓርቲ "አንድ ሕዝብ፤ አንድ ኢትዮጵያ" የሚል መርህ ያለው ፓርቲ እንደመሆኑ፣ ከዘር፣ ከጎሳ ወይም ብሄር ይልቅ በሰው ልጆች እኩልነት ያምናል፡፡ በዋናነት ከብልጽግና ፓርቲ እና ከነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ በተቃራኒ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሕዝብ መሆኑን በመግለጽ ሕዝቡ በሕገ መንግሥቱ ብሄር ወይም ብሄረሰብ ተብሎ መጠራቱን ፓርቲው ይቃወማል፡፡ ፓርቲው እንደ ኢዜማ ሁሉ የዜግነት ፖለቲካን የሚያራምድ እና ጎሳ፣ ቋንቋ እና ሐይማኖት ሳይለይ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን የቆመ ፓርቲ እንደሆነ በማያወላዳ ሁኔታ አቋሙን በፖለቲካ ፕሮግራሙ ያሠፈረ ነው፡፡ ባጠቃላይ እናት ፓርቲ በብሄር ተኮሩ ፌደራላዊ ሥርዓት ላይ ባለው አቋም ከኢዜማ ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡

ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ የፌደራላዊ ሥርዓት አራማጅ መሆኑን በፕሮግራሙ ግልጽ አድርጓል፡፡ ብሄሮች እና ብሄረሰቦች የሀገሪቱ መሠረቶች እንደሆኑ የሚናገረው ፓርቲው፣ አሁን ሥራ ላይ ያለው የፌደራላዊ ሥርዓት አወቃቀርም በዋናነት ብሄሮችን መሠረት አድርጎ መዋቀሩ ችግር አይደለም ባይ ነው፡፡ በተለይ ከኢዜማ እና እናት ፓርቲ በተቃራኒ፣ ፓርቲው በሀገሪቱ የሚከሰቱ ግጭቶች እና መፈናቀሎች መነሻቸው ብሄር ተኮሩ ሥርዓት ወይም የሥርዓቱ አወቃቀር ከተጠቀመው መርህ እንዳልሆነ ነው የሚናገረው፡፡ ይልቁንስ የችግሮቹ ዋነኛ ምንጭ ሥርዓቱ ብሄራዊ መግባባትን መፍጠር አለመቻሉ እና ሕገ መንግሥቱ ባግባቡ አለመተግበሩ እንደሆነ ነው የሚከራከረው፡፡

ነእፓ አሁን ሥራ ላይ ያለው ፌደራላዊ ሥርዓት እውነተኛ አይደለም፤ የብሄር ፌደራላዊ ሥርዓትን በትክክል መሬት ላይ አላሰፈነም ባይ ነው፡፡ ሥርዓቱ የግለሰቦችን እና ሕዳጣኖችን መብትም ማስከበር አልቻለም በማለት ይወቅሳል፡፡ በቀደሙት ሥርዓቶች የብሄር ጭቆና በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ እንደነበር የሚያምነው ፓርቲው፣ ዐላማው የብሄሮችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት የሚያከብር ጠንካራ ሕብረ ብሄራዊ ፌደራላዊ ሥርዓት መገንባት እንደሆነ ይናገራል፡፡የፌደራል ሥርዓቱ በምን መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ ይዋቀር? ለሚለው ጥያቄ፣ ነእፓ እንደ ሌሎቹ ፓርቲዎች ሁሉ የአስተዳደር ምቹነትን፣ የሕዝብ ፍላጎትን፣ ባህልን፣ መልክዓ ምድርን እና ሌሎች የጋራ እሴቶችን ታሳቢ እንደሚያደርግ ግልጽ አድርጓል፡፡ ይህ እንግዲህ የብሄር እና ቋንቋ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማለት ነው፡፡ ነእፓ ብሄር ተኮሩን ፌደራላዊ አወቃቀር በሚመለከት ያለው አቋም በተወሰነ መልኩ ከብልጽግና እና ከአብን ጋር ይቀራረባል ማለት ይቻላል፡፡

አብን እንደ ብልጽግና ፓርቲ እና ነእፓ አሁን ሥራ ላይ ያለውን ብሄር-ተኮሩን ፌደራላዊ አወቃቀር በመርህ ደረጃ የሚቀበል ፓርቲ ነው፡፡ አብን የብሄር ፖለቲካ በራሱ ችግር አይደለም የሚል አቋም አለው፡፡ እንዲያውም ባሁኗ ኢትዮጵያ የብሄር ማንነት፣ የብሄሮች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እና የብሄር ፖለቲካ የማይናቅ ሥፍራ አላቸው ብሎ ያምናል፡፡ የብሄር ፖለቲካ እና የብሄር ፌደራላዊ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ ይቀየር ቢባል እንኳ ባጭር ጊዜ ሊሳካ አይችልም ባይ ነው፡፡ አብን በዚህ በኩል ከብልጽግና ፓርቲ እና ነእፓ ጋር ተመሳሳይ አቋም ይዟል፡፡

ሆኖም አብን እንደ ነእፓ ሁሉ አሁን ሥራ ላይ ያለው ብሄር ተኮሩ ፌደራላዊ ሥርዓት በተወሰነ ደረጃ በይዘቱ እና በአተገባበሩ እውነተኛ የብሄር ፌደራላዊ ሥርዓት ገጽታ ይጎድለዋል የሚል አቋም አለው፡፡ ባንጻሩ የከፍተኛው ሕገ መንግሥታዊ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤትነት ከብሄሮችወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ መተላለፍ አለበት የሚል አቋም አለው፡፡ ሕዝቡን የከፍተኛው ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት በማድረግ ረገድ፣ አብን ከእናት ፓርቲ እና ኢዜማ የተቀራረበ አቋም የሚያራምድ ፓርቲ ነው፡፡

አብን የፌደራል አወቃቀሩ የሀገሪቱን አንድነት እና የሕዝቡን ሰላማዊ መስተጋብር ያከበረ ሆኖ እንዲደራጅ ነው የሚፈልገው፡፡ እናም እንደ አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች ሁሉ የፌደራላዊ ሥርዓቱ አወቃቀር የቦታ አቀማመጥን፣ የልማት እና አስተዳደራዊ አመችነትን፣ ታሪካዊ ባለቤትነትን፣ የሕዝብ አሠፋፈርን እና ፍላጎትን፣ መልከዓ ምድርን እና ቋንቋን በመስፈርትነት መጠቀም እንዳለበት በፕሮግራሙ ግልጽ አድርጓል፡፡

ያም ሆኖ ከሌሎች ፓርቲዎች በተለየ ለፌደራላዊ አወቃቀሩ "ታሪካዊ ባለቤትነት" እንደ መስፈርት መካተተ አለበት የሚል አቋም አለው፡፡ የዚህ ምክንያቱ ፓርቲው የሚታገልለት እና እወክለዋለሁ የሚለው የአማራ ብሄር በሀገሪቱ ውስጥ "ጥንታዊ እና ታሪካዊ" ርስቶች" አሉት ብሎ የሚል አቋም መያዙ ነው፡፡ አሁን ሥራ ላይ ያለው የፌደሬሽኑ ክልሎች አወቃቀር የአማራ ሕዝብን "ታሪካዊ መሬቶች" እና "ርስቶች" በፖለቲካ ውሳኔ ብቻ ለሌሎች ክልሎች ሰጥቷል፤ ለብሄር ከተከለለው ክልል ውጭ የሚኖሩትን የአማራ ብሄር ተወላጆች በገዛ ሀገራቸው ሁለተኛ ዜጋ አድርጓል የሚል አቋም አለው- ፓርቲው፡፡ ይህ የሆነው ሥርዓቱ ሲዋቀር የአማራ ሕዝብ በሂደቱ ተሳትፎ ባለማድረጉ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ እናም ፓርቲው የፌደራል ሥርዓቱ አዳዲስ መስፈርቶችን አካትቶ እንደገና መዋቀር አለበት የሚለው፣ ሥርዓቱ የአማራ ሕዝብን ሙሉ ተሳትፎ እና ውክልና ያረጋገጠ ሥርዓት እንዲሆን ስለሚፈልግ ነው፡፡ በፌደሬሽኑ አወቃቀር ወቅት ውዝግብ ቢነሳ፣ "ታሪካዊ ይዞታን" እና "ባለቤትነትን" ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በነጻ ሕዝበ ውሳኔ ሊፈታ እንደሚችል አብን ያምናል፡፡

### II የሕገ መንግሥት ማሻሻያ

በ1987 ዓ.ም ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ መተዳደሪያ የበላይ ሕግ ከሆነ ወዲህ መሠረታዊ ማሻሻያ አልተደረገበትም፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ ሁሉም ፓርቲዎች ስለ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ በፖለቲካ ፕሮግራማቸው አስፍረዋል፡፡ ፓርቲዎቹ በሚፈልጉት ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ መጠን እና ዐይነት ላይ ግን ልዩነቶች አሏቸው፡፡ አንዳንዶቹ ሥር ነቀል ሊባል የሚችል ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ ማድረግ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደሞ መለስተኛ ማሻሻያዎችን ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ አንዳቸውም ግን ሕገ መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ የማገድ ዐላማ የላቸውም፡፡ በርካታ ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያዎችን እናደርጋለን የሚሉት ፓርቲዎችም ቢሆኑ፣ ሕገ መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ ማገድ በሀገሪቱ የሕገ መንግሥት ቀጣይነት እንዳይኖር ያደርጋልየሚል እምነት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ኢዜማ ሥልጣን ቢይዝ አሻሽላቸዋለሁ የሚላቸው አንቀጾች በርካታ እና መሠረታዊ የሚባሉ ናቸው፡፡ ፓርቲው በፕሮግራሙ ያነሳቸው በርካታ አዳዲስ አቋሞች ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ ይፈልጋሉ፡፡ ሕገ መንግሥቱ የብሄር ፌደራላዊ አወቃቀርን እና የብሄር ፖለቲካን መከተሉ፣ የግለሰብ መብቶች የመብቶች ሁሉ ማዕዘን አለመሆናቸው፣ የብሄሮች የመገንጠል መብት እና ለብሄሮች የተሰጠውከፍተኛው ሉዓላዊ ሥልጣን፣ ኢዜማ ከሕገ መንግሥቱ ሊያስወጣቸው ከሚፈልጋቸው አንቀጾች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ባጠቃላይ በኢዜማ እምነት በሀገሪቱ መሠረታዊ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ለማምጣት ሕገ መንግሥቱ መሻሻል አለበት፡፡ ሆኖም ሕገ መንግሥቱ ራሱ ባስቀመጣቸው የማሻሻያ አንቀጾች አማካኝነት ሕገ መንግሥቱን ማሻሻል አስቸጋሪ መሆኑን ፓርቲው ይገልጣል፡፡ ይህንኑ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በቅድሚያ ሕገ መንግሥቱን ማሻሻል ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም? የሚለውን ጥያቄ ለሕዝበ ውሳኔ አቀርበዋለሁ ብሎ ቃል ገብቷል፡፡ የሕዝበ ውሳኔው ውጤት አወንታዊ ከሆነ፣ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሳቦቹን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለሚዋቀር ሕገ መንግሥታዊ ኮሚሽን እንደሚያቀርብ ከወዲሁ አቋም ይዟል፡፡

ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ ከመነሻው አሁን ሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት ለዘመናት ሲንከባለሉ ለቆዩት የመደብ እና የብሄር ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በሚያስችል አኳኋን የተቀረጸ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ነእፓ በዚህ አቋሙ በዋናነት ከብልጽግና ፓርቲ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ሆኖም ሕገ መንግሥቱን ከሀገራዊ እና ዐለማቀፋዊ ሁኔታዎች እና ለውጦች ጋር ማጣጣም አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጸው ነእፓ፣ ሕገ መንግሥቱ አሁን ባለበት ደረጃ ሳይሻሻል ከቆየ ውሎ አድሮ በሃይል የመለወጥ አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል ስጋቱን ያስቀምጣል፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ ፓርቲው ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል እንደሚታገል ወይም ሥልጣን ከያዘ ደሞ እንደሚያሻሽለው በፖለቲካ ፕሮግራሙ ግልጽ አድርጓል፡፡

ነኢፓ ከሕገ መንግሥቱ መሻሻል አለባቸው የሚላቸውን ጠቅለል ያሉ ነጥቦች አስቀምጧል፡፡ ሰላም እና ደኅንነትን የሚሸረሽሩ እና መገንጠልን የሚጋብዙ አንቀጾች ብሄራዊ መግባባትን በሚፈጥር መልኩ እንዲሻሻሉ ፓርቲው ፍላጎት አለው፡፡ ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እና ግዛት አንድነት በማይሸረሽር መልኩ እንዲሻሻል፣ ከአጠቃላይ ዕድገት ደረጃ አንጻር በየጊዜው ሊቀየሩ የሚችሉ አንቀጾች ከሕገ መንግሥቱ እንዲወጡ፣ ሕገ መንግሥቱ የአብዛኛውን ኅብረተሰብ ፖለቲካ አመለካከት ግምት ውስጥ ያስገባ እና ከገዥ ፓርቲ ፕሮግራምነት የተላቀቀ እና በቋንቋ፣ በክልሎች አመሠራረት እና ወሰን ላይ አላስፈላጊ ልዩነት ለሚፈጥሩ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጥ ሆኖ መሻሻል አለበት የሚል እምነትም አለው፡፡ ለብሄር ብሄረሰቦች ስስ ልብ ያለው ፓርቲው፣ የብሄሮች የመገንጠል መብት ግን ለሕዝብ ውይይት ለማቅረብ ነው አቋም የያዘው፡፡ የዚህም ምክንያቱ ፓርቲው ሕገ መንግሥታዊ የማሻሻያ ሃሳብን ከማመንጨት ጀምሮ እስከ ማሻሻል ድረስ ሂደቱ ሕዝብን ያሳተፈ እንዲሆን ስለሚፈልግ እንደሆነ በማንፌስቶው ላይ አብራርቷል፡፡

እናት ፓርቲ እንደ ኢዜማ ሁሉ የዜግነት ፖለቲካ አራማጅ በመሆኑ፣ በርካታ ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ የሚፈልግ የፖለቲካ ፕሮግራም ያለው ፓርቲ ነው፡፡ ፓርቲው ሕገ መንግሥቱን በሕዝበ ውሳኔ ለማሻሻል እንደሚታገል በፕሮግራሙ የጠቀሰ ሲሆን፣ የሕዝብ ይሁንታን አግኝቶ ሥልጣን ቢይዝ የመጀመርያ ሥራው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ማድረግ እንደሆነ ግልጽ አድርጓል፡፡ እናት ፓርቲ የሕገ መንግሥቱ ገዥ ሃሳብ ያንድ ፓርቲ ርዕዮተ ዐለም እና የፖለቲካ ፕሮግራም እንዳይሆን፣ የሁሉንም ሕዝቦች ጥቅም እና ፍላጎቶች እንዲያቻችል እና ዘለግ ላለ ጊዜ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጎ መሻሻል አለበት ባይ ነው፡፡

አብን በበኩሉ መሠረታዊ የሕገ መንግሥት ማሻሻያዎች እንዲደረጉ የሚፈልገው ባብዛኛው ከሚወክለው የአማራ ሕዝብ ጥቅም አንጻር ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱ በአማራ ሕዝብ ዘንድ ቅቡልነት እንደሌለው በመጥቀስ፣ ፓርቲው 15 የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሳቦችን ያካተተ ሰነድ ይፋ አድርጓል፡፡ ሕገ መንግሥቱ የአማራ ሕዝብን "ታሪካዊ ግዛቶች" የከፋፈለ፣ የሕዝቡን ማንነት፣ ቋንቋ፣ ባህል እና የኢኮኖሚ መብቶችን ያላስከበረ እና መንፈሱ በጸረ-አማራ ትርክት የተቃኘ እንደሆነ በመግለጽ መሻሻል እንዳለበት ቁርጠኛ አቋም ይዟል፡፡ ፓርቲው ለብሄረሰቦች ሰፊ እውቅና እና መብት የሚሰጥ ቢሆንም፣ እንደ ኢዜማ እና እናት ፓርቲ ሁሉ የመገንጠል መብት ከሕገ መንግሥቱ መውጣት አለበት የሚል አቋም አለው፡፡

በሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ ላይ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ሲነጻጸር የተብራራ አቋም የሌለው ብልጽግና ፓርቲ ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱ የተለያዩ ጥያቄዎች እንደሚነሱበት የሚጠቅሰው ፓርቲው፣ በደፈናው ሕገ መንግሥቱ በተረጋጋ እና አመቺ በሆነ ጊዜ እንጅ  በጥድፊያ መሻሻል የለበትም ይላል፡፡፡፡ ፓርቲው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ አስፈላጊነትን ዝግ ባያደርገውም፣ ለወደፊቱ እንዲሻሻሉ የሚፈልጋቸውን የሕገ መንግሥት አንቀጾች ግን በፖለቲካ ፕሮግራሙ አብራርቶ አላስቀመጠም፡፡ ያም ሆኖ ሕገ መንግሥቱ ወደፊት ሲሻሻል በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡትን ማሻሻያ አንቀጾች ወይም ሌሎች ዐለማቀፋዊ ልምዶችን መጠቀም እንደሚቻል ፓርቲ በፕሮግራሙ ጠቅሷል፡፡ ይህ የብልጽግና አቋም የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ውሳኔን ለሕዝበ ውሳኔ እናቀርባለን ከሚሉት ኢዜማ እና እናት ፓርቲ የተለየ ነው፡፡

ባጠቃላይ ብልጽግና ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች የሚለየው፣ ምርጫውን አሸንፎ በመንግሥትነቱ ቢቀጥል እንኳ በሥልጣን ዘመኑ ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል ቁርጥ ያለው አቋም ያልያዘ ፓርቲ መሆኑ ነው፡፡

### III የኢኮኖሚ ፖሊሲ

የፓርቲዎች ኢኮኖሚ ፖሊሲ ግብርናን፣ ኢንዱስትሪን፣ አምራች ዘርፉን፣ አገልግሎት ዘርፉን፣ መሬትን እና ተፈጥሮ ሃብትን፣ ከተማ ልማትን፣ መሠረተ ልማትን፣ መንግሥት፣ የግል እና የውጭ ባለሃብቶች በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና፣ ፋይናንስን እና በጀትን የመሳሰሉ ንዑስ ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ በዚህ ሪፖርት ለንጽጽር ጥቅም ላይ የዋሉት ግን፣ የፓርቲዎቹ ዋና ዋና የኢኮኖሚ መርሆዎች እና በተለይ ደሞ ለበርካታ ዐመታት የኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ጥያቄም ሆኖ የቆየው የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ ብቻ ናቸው፡፡

በዚህ ሪፖርት የተጠቀሱት ሁሉም ፓርቲዎች በዋናነት ገበያ መር የኢኮኖሚ ፍልስፍና አራማጆች ናቸው፡፡ ፓርቲዎቹ በበርካታ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ተመሳሳይ መርሆዎች እና አቋሞች አሏቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉም ፓርቲዎች አስፈላጊ በሆኑ የተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ይፈቅዳሉ፡፡ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ዋነኛ የኢኮኖሚው

አንቀሳቃሽ ሞተር እንዲሆን እና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲመጣ ይፈልጋሉ፡፡ ሁሉም ፓርቲዎች ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረት (import substitution) ቅድሚያ የሚሰጡ ናቸው፡፡ በመሬት ፖሊሲ ረገድም፣ አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች መሬት የመንግሥት፣ የግል እና የማኅበረሰብ ተብሎ በሦስት መደልደል እንዳለበት ይስማማሉ፡፡

ኢዜማ የኢኮኖሚ ፖሊሲው ከማኅበራዊ ፍትህ የፖለቲካ ርዕዮተ ዐለሙ የሚመነጭ እንደሆነ በተለያዩ ሰነዶቹ ገልጧል፡፡ የፓርቲው የማኅበራዊ ፍትህ ፍልስፍና ዐላማ ደሞ፣ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ነጻነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሆነ ተብራርቷል፡፡ ፓርቲው ገበያ መር የኢኮኖሚ መርህ የሚከተል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢኮኖሚው ወደ ዳር የገፋቸውን እና ለድህነት የተዳረጉ ዜጎችን የሚታደግ ልዩ ፖሊሲ ግን ነድፎ ሥራ ላይ የማዋል ዐላማ አለው፡፡

ለኢዜማ በመርህ ደረጃ ዋነኛው የምጣኔ ሃብት አንቀሳቃሽ ሞተር የግሉ ዘርፍ ነው፡፡ ከፍተኛ ሥራ አጥነት ሲኖር፣ የምጣኔ ሃብት ማሽቆልቆል ሲያጋጥም፣ የዋጋ ግሽበት እና የበጀት ጉድለት ሲከሰት ግን መንግሥት በኢኮኖሚው ጣልቃ ገብቶ ገበያውን እንዲያረጋጋ ይፈቅዳል፡፡ ከፍተኛ ሙዓለ ንዋይ በሚጠይቁ፣ አዋጭነታቸው አጠያያቂ በሆኑ፣ በረጅም ጊዜ ብቻ ጥቅም በሚያስገኙ የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ መንግሥት ለብቻው ወይም ከግሉ ዘርፍ ጋር በሽርክና መሠረተ ልማቶችን መገንባት እንዳለበት የፓርቲው አቋም ነው፡፡ የፓርቲው ፖሊሲ መንግሥት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን እንዲያቋቁም እና እንዲያስተዳድርም ይፈቅዳል፡፡

ኢዜማ የመሬት እና ተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀም የነጻ ገበያ ኢኮኖሚን እና የሀገር ሉዓላዊነትን ባስጠበቀ መልኩ እንዲሆን የሚታገል ፓርቲ ነው፡፡ ፓርቲው አሁን ሥራ ላይ ያለው መሬት በመንግሥት ይዞታ ስር መሆኑን የሚፈቅደው ፖሊሲ በሀገሪቱ የምጣኔ ሃብት ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል የሚል እምነት አለው፡፡ ይህንኑ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የመሬት ይዞታ ወይም ባለቤትነት በመንግሥት፣ በማኅበረሰቡ ወይም በግል ሊሆን እንደሚችል ፓርቲው በፕሮግራሙ ግልጽ አድርጓል፡፡ ሕዝብ ያልሠፈረባቸው፣ ፓርኮች እና ለመንግሥት አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎች ግን በመንግሥት ይዞታ ሥር ሊሆኑ እንደሚችሉ ፓርቲው ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ እና ሌሎች በመንግሥት ይዞታ ሥር ያሉ ቦታዎች በግልጽ መስፈርት እና በነጻ ገበያ ዋጋ ወደ ግል እንዲዛወሩ ወይም በሊዝ ለውጭ ባለሃብቶች እንዲከራዩ ፓርቲው ይፈቅዳል፡፡ በተለይ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ አለማደግ ዋነኛው ምክንያት ትክክለኛ የመሬት ፖለሲ አለመኖሩ እንደሆነ የሚገልጸው ኢዜማ፣ ዜጎች መሬትን በግል ይዞታነት እና ባለቤትነት የመያዝ፣ የማከራየት፣ የመግዛት፣ የመሸጥ እና መለወጥ መብት እንዲኖራቸው የሚፈቅድ ፖሊሲ ይከተላል፡፡ ይህ የፓርቲው አቋም ከአርባ ዐመታት በላይ በሀገሪቱ ሲተገበር ከቆየው የመሬት ፖሊሲ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡

ብልጽግና ፓርቲም እንደ ኢዜማ ሁሉ ገበያ መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚከተል ፓርቲ ነው፡፡ በመንግሥት፣ በግል ባለሃብቶች እና በመንግሥት እና በግል ባለሃብቶች ትብብር ጥራት ያላቸው መሠረተ ልማቶች እንዲገነቡ ጠንክሮ እንደሚሠራ ፓርቲው በፕሮግራሙ ገልጧል፡፡ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ሚና ማሳደግ ዐላማው እንደሆነ የሚጠቅሰው ፓርቲው፣ በመንግሥት ይዞታ ሥር ያሉ ድርጅቶች ወደ ግል ዘርፉ እንዲሸጋገሩ እንደሚያደርግ፣ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን እንደሚተገብር እና ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን እንደሚነድፍ ቃል ገብቷል፡፡

እናት ፓርቲ የኢኮኖሚ ፍልስፍናው እንደ ሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ ነጻ ገበያ እንደሆነ ያስቀምጥና፣ አስፈላጊ በሆኑ ዘርፎች ግን በኢኮኖሚው ውስጥ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት እንዲኖር እንደሚፈቅድ ይገልጻል፡፡ መንግሥት ትላልቅ መሠረተ ልማቶችን የመገንባት ሃላፊነት እንዳለበት ፓርቲው ያምናል፡፡ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ቀደም ሲል ተጠቃሚ ላልሆኑ እና ትኩረት ለተነፈጋቸው ዜጎች እና አካባቢዎች ቅድሚያ መስጠት አለበት የሚል አቋምም አለው፡፡ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው እና በታሪክ መድልዖ እና መገለል ለደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችም ልዩ ጥቅሞችን የሚያስገኙ የምጣኔ ሃብት ፖሊሲዎችን እነድፋለሁ ይላል፡፡ ማኅበራዊ ፍትህን እና ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን አሰፍናለሁ በሚለው አቋሙ፣ ፓርቲው ከኢዜማ ጋር ይቀራረባል ማለት ይቻላል፡፡

እናት ፓርቲ ብዙ ችግር አለበት ለሚለው የመሬት ፖሊሲ ስር ነቀል መፍትሄ እሰጣለሁ ባይ ነው፡፡ በነባሩ መሬት ፖሊሲ ምትክ አዲስ ፖሊሲ እንደሚነድፍ አቋሙን ግልጽ ያደረገው ፓርቲው፣. መሬትን የመንግሥት፣ የግል እና የማኅበረሰብ ይዞታ በማለት በሦስት እንደሚደለድል ለሕዝቡ አሳውቋል፡፡ ፓርቲው የአርሶ አደሩን የመሬት ባለቤትነት መብት ሙሉ በሙሉ እንደሚያጎናጽፍም ቃል ገብቷል፡፡

ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲም እንደ ሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓትን የሚከተል ሲሆን፣ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በሚያስፈልግባቸው መስኮች ግን የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት የሚፈቅድ ፓርቲ ነው፡፡ ግዙፍ መሠረተ ልማቶችን መንግሥት ብቻውን ወይም ከግል ባለሃብቶች ጋር በሽርክና መገንባት እንዳለበት ፓርቲው ያምናል፡፡ በዜጎች እና ክልሎች መካከል ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን የሚፈጥር ፖሊሲ እንደሚከትልም በፕሮግራሙ ገልጧል፡፡

ነእፓ የመሬት ይዞታ እና ባለቤትነት ከፖለቲካ፣ ባህል፣ ስነ ሕዝብ እና አካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዘ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ ፓርቲው በከተማም ሆነ በገጠር ያለው መሬት የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት እንደሆነ ይገልጽና፣ መሬትን የማስተዳደር ሃላፊነት ግን የመንግሥት መሆን አለበት ይላል፡፡ እንደ ኢዜማ መሬትን የመሸጥ እና መለወጥ መብትን ባይፈቅድም፣ አርሶ አደሮች ለእርሻ የሚጠቀሙትን መሬት የማከራየት መብት እንዲኖራቸው ግን ይፈቅዳል፡፡፡፡ ለአርሶ አደሮች እና መኖሪያ ቤት ለሚሠሩ የከተማ ነዋሪዎች የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ እሰጣለሁ፤ በመሬቱ ላይ ያላቸው ጥቅም በሕግ እንዲጠበቅላቸው አደርጋለሁ ይላል፡፡ ፓርቲው ምንም እንኳ መሬትን የመሸጥ እና መለወጥ መብትን ለጊዜው ባይፈቅድም፣ የሀገሪቱን ዕድገት ባገናዘበ መልኩ በሂደት የሚታይበትን የፖሊሲ አቅጣጫ ግን እከተላለሁ ይላል፡፡

እንደሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ የአብንም የኢኮኖሚ መርህ ገበያ መር ነው፡፡ የፓርቲው ኢኮኖሚ መርህ አሁን በሀገሪቱ ሥራ ላይ ያለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ የአማራን ሕዝብ ምጣኔ ሃብት ሆን ብሎ እንዲገታ አድርጓል የሚል መነሻ አለው፡፡ የውጭ ንግድን እና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በመንግሥት ይዞታ ሥር ያሉ አትራፊ ተቋማት እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ግል ባለሃብቶች ሊዛወሩ እንደሚችሉ ፓርቲው አቋሙን በፕሮግራሙ አስፍሯል፡፡ መንግሥት ገበያን ለማረጋጋት ዐላማ እና ከፍተኛ በጀት በሚጠይቁ የልማት ሥራዎች ሊሰማራ ይገባዋል የሚለው የፓርቲው አቋም ነው፡፡ መንግሥት ትላልቅ ድርጅቶች የሚከፍሉትን ግብር በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በሚጠቅሙ ኢንቨስትመንቶች ሊያውለው እንደሚችልም ፓርቲው ያስቀምጣል፤ ይፈቅዳልም፡፡

አብን እንደ ሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ የመሬት ባለቤትነት የግል፣ የመንግሥት እና ኅብረተሰብ ተብሎ በሦስት እንዲከፈል ይፈልጋል፡፡ “የአማራው ‘ታሪካዊ መሬቶች’ ባለቤት የአማራ ሕዝብ ነው” ከሚለው የፓርቲው አቋም ጋር በማይጣረስ መልኩ፣ የገጠርንም ሆነ የከተማ የግል መሬት ይዞታን መሸጥ፣ መለወጥ እና ለሦስተኛ አካል በውርስ ማስተላለፍን የፓርቲው ፖሊሲ ይፈቅዳል፡፡ አብን ጥብቅ ደኖች፣ ፓርኮች፣ ተራሮች፣ ሐይቆች እና ወንዞች ያሉባቸው መሬቶች በመንግሥት ይዞታ ሥር እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡

## IV የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ

ፓርቲዎቹ በውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ረገድ መሠረታዊ የሚባል ልዩነት የላቸውም፡፡ ሁሉም ከውስጥ ወደ ውጭ የሚመለከት የውጭ ፖሊሲ የሚያራምዱ ፓርቲዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉም የዜጎችን እና የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅሞች ቅድሚያ የሚሰጥ ፖሊሲ እንደሚቀርጹ ነው በፕሮግራማቸው የሚገልጹት፡፡

የኢዜማ ውጭ ፖሊሲ የመሠረታዊ ሀገራዊ ደኅንነት አደጋዎች መነሻ ከውጣዊ ችግሮች እንደሆነ ያምናል፡፡ ኢትዮጵያ ብሄራዊ ደኅንነቷን ለማስከበር ከሚጠቅሟት ሀገሮች ጋር ግንኙነት እንድትመሰርት እና ጥቅሟን ከሚጻረሩት ደሞ ራሱን ለመከላከል የሚያስችላትን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እንደሚቀርጽ ፓርቲው በፕሮግራሙ ገልጧል፡፡ ኢዜማ እከተለዋለሁ የሚለው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በጋራ ተጠቃሚነት፣ ልማት እና ሰላም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንደሚሆን እና ግንኙነቱ ከጋራ ኢኮኖሚ ግንባታ እስከ ጋራ መከላከያ ሃይል ምስረታ ሊደርስ እንደሚችል ያብራራል፡፡ የተለያዩ የዐለም ኃያላን በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶች እንዳላቸው እና የቀጠናው ሀገራት ተለዋዋጭ አሰላለፍ የሚከተሉ እንደሆኑ የሚገልጸው ኢዜማ፣ ለየሀገራቱ የተናጥል የውጭ ፖሊሲ እቀርጻለሁ ይላል፡፡ኢትዮጵያ አፍሪካ ኅብረት ጠንክሮ እንዲወጣ እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዐለማቀፍ ፍትህ አካል እንዲሆን ጥረት እንድታደርግ የሚያስችላትን ፖሊሲ እንደሚከተል እንዲሁም ሀገሪቱ ለሰው ልጆች ሰላም፣ መብቶች፣ አካባቢ ጥበቃ እና ዕድገት ከሚሠሩ ዐለማቀፍ ድርጅቶች ጋር በቅርበት እንድትሰራ የሚያደርግ ፖሊሲ እንደሚነድፍ ፓርቲው ይገልጻል፡፡

ኢዜማ የባሕር በር መብትን ከኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን፣ ከብሄራዊ ደኅንነት እና ሀገራዊ ሕልውና አንጻር የሚያይ ፓርቲ ነው፡፡ ፓርቲው ባንድ የጎረቤት ሀገር ወደብ ላይ መወሰን ኢትዮጵያን ለብሄራዊ ደኅነንት ስጋት ያጋልጣታል የሚል እምነት አለው፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ፣ ኢትዮጵያ ባለቤት ሆና የምታስተዳድረው የባሕር በር እና መተላለፊያ ኮሪደር የማግኘት መብት እንዲኖራት እና ይህንኑ መብቷን በሕጋዊ እና ዲፕሎማሲያዊ መንገድ እንድታስከብር እንደሚታገል ፓርቲው በፕሮግራሙ አስፍሯል፡፡

ብልጽግና ፓርቲ በበኩሉ የሀገሪቱን አንድነት እና የዜጎቿን ክብር የሚያንጸባርቅ፣ ብሄራዊ ክብርን እና ጥቅምን የሚያስጠብቅ የተማከለ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እንደሚቀርጽ በፕሮግራሙ ግልጽ አድርጓል፡፡ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው ግቦች፣ ብሄራዊ ክብርን ማረጋገጥ፣ ፓን አፍሪካኒዝምን ማጠናከር፣ ለትብብር እና የጋራ ተጠቃሚነት ትልቅ ትኩረት መስጠት፣ አጋሮችን ማብዛት፣ ለየትኛው የዐለም ኃያላን ዋልታ ያልወገነ ዲፕሎማሲ መከተል፣ የፖሊሲ ነጻነትን ማረጋገጥ፣ ከጉረቤት ሀገራት ጋር አካባቢያዊ የልማት፣ ኢኮኖሚ እና ሰላም ትስስር መፍጠር፣ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አጠቃቀም በዐለማቀፍ መርሆዎች እንዲሆን ማድረግ እና ከባለ ወደብ ሀገሮች የተሻለ የወደብ ተጠቃሚነት መብት ማግኘት ወዘተ ናቸው ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡

እናት ፓርቲ በበኩሉ የውጭ ግንኙነት መርሆው የሚመሠረተው ሀገሪቱ ዲሞክራሲ፣ አስተማማኝ ሰላም እና ዘላቂ ልማት ለመፍጠር ባላት ውስጣዊ አቅም ላይ እንደሆነ የሚገልጽ ፕሮግራም አለው፡፡ እንደ ሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ ፓርቲው የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እና ብሄራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ፖሊሲ ቀርጾ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ይናገራል፡፡ በዐለማቀፍ ግንኙነት ውስጥ ኢፍትሃዊነት እንዲወገድ፣ በታዳጊ ሀገሮች ላይ የሚደረጉ ዐለማቀፍ ጫናዎች እንዲቀሩ እና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲፈጠር እንደሚታገል ፓርቲው በፕሮግራሙ አብራርቷል፡፡

የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ ዐለማቀፉ ኅረተሰብ እንደሚገነዘበው የሚጠቅሰው ፓርቲው፣ ልክ እንደ ኢዜማ ሁሉ ጉዳዩ ከሀገራዊ ሕልውና እና ሉዓላዊነት ጋር የተያያዘ ሕጋዊ ጥያቄ መሆኑን የሚያምን ፓርቲ ነው፡፡ እናም ፓርቲው ለችግሩ መፍትሄ ብሎ ያስቀመጠው፣ የባሕር በር ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ እና ከጎረቤት ኤርትራ ጋር በሚደረግ ስምምነት መፍትሄ እንዲያገኝ ጥረት አደርጋለሁ የሚል ነው፡፡

ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ በበኩሉ የሚቀርጸው የውጭ ፖሊሲ ግቡ የሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ዕቅዶችን ለማሳካት የሚያግዝ እንደሚሆን ይጠቅሳል፡፡ የውስጥ ሰላምን አስተማማኝ ለማድረግ በቅድሚያ አካባቢያዊ ሰላም የሚፈጥር ፖሊሲ መንደፍ አስፈላጊ መሆኑን የሚያምነው ፓርቲው፣ ድንበር ተሻጋሪ ችግሮችን፣ ስጋቶችን እና ተግዳሮቶችን በጋራ ለመፍታት የሚያስችል ፖሊሲ እነድፋለሁ ይላል፡፡ በሀገራት ውስጣዊ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፣ መተማመን እና መከባበር ላይ የተመሠረተ ፖሊሲ እንደሚተገብርም ያብራራል፡፡ ኢትዮጵያ አፍሪካ ኅብረትን እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን በመጠቀም ብሄራዊ ጥቅሞቿን እንድታስጠብቅ የሚያደርግ እና ለነጻው አሕጉራዊ የንግድ ቀጠና ድጋፍ የሚሰጥ ፖሊሲ እንደሚኖረው ፓርቲው አክሎ በፕሮግራሙ ላይ ገልጧል፡፡

ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ በኢኮኖሚ፣ ዲፕሎማሲ፣ ወታደራዊ እና ቴክኖሎጅ ዘርፍ ከፍተኛ አቅም ካላቸው ሀገሮች ጋር ኢትዮጵያ ለሚኖራት ግንኙነት ትኩረት እንደሚሰጥ በፕሮግራሙ ጠቅሷል፡፡ ኢትዮጵያ ወደተወሰኑ የዐለም መንግሥታት የምታደርገው ሚዛኑን ያልጠበቀ ማጋደል ብሄራዊ ጥቅሟን እንደሚጎዳው በመጥቀስ፣ ሥልጣን ቢይዝ ይህን አዝማሚያ እንደሚያስተካክል ፓርቲው በማኒፌስቶው ገልጧል፡፡ ሀገሪቱ በእነዚህ እና ሌሎች መስኮች የተዋጣለት ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እንድታደርግ ፓርቲው ሙያተኛ እና የዳበረ ልምድ ያላቸው ዲፕሎማቶችን ለማሰማራት ቁርጠኛነቱን ይገልጣል፡፡ በተለይ ከአፍሪካ ቀንድ ቀጠና የሚነሱ ስጋቶችን ለመመከት ሀገሪቱ ወታደራዊ ኃይሏን እና የጸጥታ ተቋሞቿን እንድታጠናክር የሚያደርግ ፖሊሲም ይኖረዋል፡፡

አብን የውጭ ግንኙነት መርሆዎቹ የሀገር እና ሕዝብ ዘላቂ ጥቅምን በማስከበር ላይ እንደሚመሰረቱ በፕሮግራሙ አስፍሯል፡፡ የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅሞች የማያስከብሩ ዐለማቀፍ ውሎች እና ስምምነቶች እንዲሻሻሉ ወይም እንዲሰረዙ እንደሚያደርግ ፓርቲው ይገልጣል፡፡ አብን የሀገሪቱ ባሕር በሮች ካሁን ቀደም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለሌላ ሀገር ተላልፈው ተሰጥተዋል የሚል አቋም አለው፡፡ ይህን አቋሙን መሠረት በማድረግ፣ ኢትዮጵያ ባሕር በሮቿን በሰላማዊ እና ሕጋዊ መንገድ የማስመለስ መብት እንዳላት አብን ያምናል፡፡ ይህንኑ እምነቱን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል የውጭ ፖሊሲ እንዲነደፍ ትግል እንደሚያደርግ አቋሙን ግልጽ አድርጓል፡፡

## V የአዲስ አበባ ከተማ ባለቤትነት ጥያቄ እና አስተዳደራዊ ዕጣ ፋንታ

አዲስ አበባ ሙሉ በሙሉ በኦሮሚያ ክልል ግዛት ውስጥ መገኘቷ፣ ከፌደራል መንግሥቱ በተጨማሪ የኦሮሚያ ክልል መቀመጫ መሆኗ፣ ኦሮሚያ ክልል ከተማዋ ላይ ያለው ሕገ መንግሥታዊ "ልዩ ጥቅም" እና ከተማዋ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካ ማዕከል መሆኗ፣ በርካታ ተቃራኒ የፖለቲካ ፍላጎቶች እንዲንጸባረቁባት አድርጓታል፡፡ ከተማዋ ላይ እስካሁን መፍትሄ ያላገኘ የተካረረ የባለቤትነት ጥያቄ የሚነሳባትም ለዚሁ ነው፡፡

በከተማዋ እና ኦሮሚያ ክልል መካከል የሚነሳው የአስተዳደር ወሰን ውዝግብ እና የከተማዋ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄም ቁልፍ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በርግጥ ከተማዋ ራሷን በራሷ እንድታስተዳድር ሕገ መንግሥቱ ሥልጣን ሰጥቷታል፡፡ ሆኖም የከተማዋ ተጠሪነት ለፌደራል መንግሥቱ በመሆኑ ሥልጣኗን እስካሁን በተሟላ አኳኋን ልትተገብረው አልቻለችም፡፡

የከተማዋ የባለቤትነት እና አስተዳደራዊ ችግሮች እና ውዝግቦች እየተካረሩ መሄዳቸው፣ ባለፉት ጥቂት ዐመታት ከተማዋ ራስ ገዝ እንድትሆን የሚታገለው እና ዋና ትኩረቱን አዲስ አበባ ላይ ያደረገው ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ እንዲወለድ ምክንያት ሆኗል፡፡ በዘንድሮው ጠቅላላ ምርጫም የከተማዋ ባለቤትነት፣ አስተዳደራዊ አወቃቀር እና አስተዳደራዊ ውዝግቦች ቁልፍ አጀንዳ ሆነዋል፡፡ ለእነዚህ በከተማዋ ዙሪያ ለሚነሱ ችግሮች፣ በዚህ ሪፖርት የተካተቱትን ፓርቲዎች ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ ኃይሎች የየራሳቸውን አማራጮች ያቀርባሉ፡፡

ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ በማንፌስቶው የአዲስ አበባን ባለቤትነት ጉዳይ በተመለከተ ንድፈ ሃሳቦችን እና የሌሎች ሀገሮችን ልምዶች እያጣቀሰ ሰፊ ትንታኔ ሰጥቶበታል፡፡ የተለያዩ ፌደራላዊ ሀገሮች ለዋና ከተማቻቸው የሚከተሏቸው አስተዳደራዊ አወቃቀሮች ምን ጥቅሞች እና ጉዳቶች እንዳሏቸው በሰፊው ዘርዝሯል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ የሚንጸባረቁት ፍላጎቶች፣ የከተማዋ ነዋሪ ራስን በራስ የማስተዳደር ፍላጎት፣ የፌደራል መንግሥት ፍላጎት እና ከከተማው ጋር ድንበር የሚጋራው የኦሮሚያ ክልል ፍላጎት መሆናቸውን ፓርቲው ይገልጻል፡፡

ፓርቲው ለጉዳዩ ያስቀመጠው ገዥ መርህ፣ የከተማዋ አስተዳደራዊ ቅርጽ የነዋሪዎቿን፣ የፌደራል መንግሥቱን እና የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎቶች የሚያስታርቅ እና የነዋሪዎቿን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት ቅድሚያ የሚሰጥ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ የከተማዋ አስተዳደራዊ እና ባለቤትነት ውዝግቦች የነዋሪዎቿን፣ የሁሉም ኢትዮጵያዊያንን፣ በዙሪያዋ ያሉ አርሶ አደሮችን እና አሕጉራዊ ጥቅሞችን በሚያማክል ሕጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲታይ ፓርቲው ይፈልጋል፡፡ አስተዳደራዊ ጥያቄው ነዋሪዎቿን ተጠቃሚ በሚያደርግ እና ጠንካራ ፌደራል መንግሥት እንዲኖር በሚፈቅድ ሁኔታ መፈታት አለበት የሚል አቋምም አለው፡፡ ፓርቲው ሥልጣን ቢይዝ፣ በከተማዋ ዙሪያ የሚኖሩ አርሶ አደሮች ሳይፈናቀሉ የከተማዋ ነዋሪ የሚሆኑበትን ወይም ከመንግሥት በቂ ካሳ የሚያገኙበትን አሠራር እንደሚዘረጋ ቃል ገብቷል፡፡ ይህ አካሄድ አርሶ አደሮች የከተማዋን መስፋፋት እንደ ዕድል እንጅ እንደ ስጋት እንዳያዩት እንደሚያደርግ እና ይህንኑ ለመተግበር ሕጋዊ ማዕቀፍ እንደሚዘረጋ ፓርቲው በፕሮግራሙ አብራርቷል፡፡

ከተማዋ ላይ የሚነሳውን ውዝግብ ለማቃለል ሌላው ፓርቲው አማራጭ ብሎ ያስቀመጠው መፍትሄ፣ ሁለት እና ከዚያ በላይ ተጨማሪ ዋና ከተሞችን በተለያዩ ክልሎች ማቋቋም ነው፡፡

እናት ፓርቲ አዲስ አበባ ከተማ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ከተማ መሆኗን የሚቀበል ፓርቲ ሲሆን፣ በከተማ ማንም የተለየ የባለቤትነት ጥያቄ ሊያነሳባት አይችልም የሚል አቋም አለው፡፡ ሕገ መንግሥቱ አዲስ አበባ ላይ ለኦሮሚያ ክልል በተለይ የሰጠውን የ"ልዩ ጥቅም" አንቀጽም ፓርቲው አይቀበልም፡፡ ፓርቲው ሥልጣን ቢይዝ መሠረታዊ የሕገ መንግሥት ማሻሻያዎችን ማድረግ የሚፈልግ በመሆኑ፣ ይህንኑ የ"ልዩ ጥቅም" አንቀጽም ያኔ እንደሚያስወጣው ይናገራል፡፡

የከተማዋ ችግር ለፌደራል መንግሥቱ ተጠሪ ከመሆኗ እና በፌደራል መንግሥቱ ውክልና የሌላት ከመሆኑ የሚመነጭ እንደሆነ የሚገልጸው እናት ፓርቲ፣ በዚህ የተነሳ አሁን ባለው አስተዳደራዊ አወቃቀር የከተማዋ ነዋሪዎች የፖለቲካ እና ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በጣም የተገደበ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ ፓርቲው በከተማዋ ላይ ለሚነሱት የባለቤትነት ጥያቄዎች እና

አስተዳደራዊ ውዝግቦች ያስቀመጠው ስር ነቀል አስተዳደራዊ መፍትሄ አዲስ አበባን ራሷን የቻለች የፌደሬሽኑ አባል ክልል ማድረግ ነው፡፡

ኢዜማ የአዲስ አበባ ከተማን ምርጫ ቢያሸንፍ የከተማዋን ቁልፍ ችግሮች እፈታበታለሁ ያለውን ራሱን የቻለ የቃል ኪዳን ሰነድ አዘጋጅቷል፡፡ በኢዜማ እምነት ከተማዋ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የመጡ ኢትዮጵያዊያን የገነቧት እና አሁንም የሚኖሩባት ከተማ ናት፡፡ እናም የአዲስ አበባ ባለቤት ማነው? ለሚለው ጥያቄ፣ ፓርቲው የከተማዋ ባለቤት በዋናነት ነዋሪዎቿ ናቸው የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡ አስተዳደርን በተመለከተ ከተማዋ ራሷን በራሷ የምታስተዳድርበትን ሥርዓት እንደሚዘረጋ እና ይህንኑ መብቷን ሳይሸራርፍ እንደሚያስከብር ፓርቲው በቃል ኪዳን ሰነዱ ላይ አስፍሯል፡፡ ፓርቲው የአዲስ አበባ ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን ማጠናከሩ እና ማስፋቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሁን ያላት ሕገ መንግሥታዊ አስተዳደራዊ አወቃቀር ማለትም ከተማዋ ተጠሪነቷ ለፌደራሉ መንግሥት መሆኑ ግን ባለበት እንዲቀጥል ነው የሚፈልገው፡፡

ኢዜማ ከተማዋ የታወቀ አስተዳደራዊ ወሰን ሳይኖራት መቆየቱ ሁለንተናዊ ዕድገቷን እንዳጓተተው ያምናል፡፡ በተለይ ኦሮሚያ ክልል ከአዲስ አበባ ጋር በሚያነሳው የወሰን ይገባኛል ጥያቄ ሳቢያ በከተማዋ ላይ የደኅንነት ስጋት ተፈጥሯል ባይ ነው፡፡ እናም ከተማዋ በሕግ የታወቀ አስተዳደራዊ ወሰን እንዲኖራት ፓርቲው ከፌደራል እና ከኦሮሚያ ክልል ጋር በቅንጅት እንደሚሰራ ይናገራል፡፡ ፓርቲው ለችግሩ መፍትሄ የሚያዘጋጀው ግን፣ የከተማዋን እና የነዋሪዎቿን ጥቅም ባረጋገጠ እና ከተማዋ የፌደራል መንግሥቱ መቀመጫ መሆኗን ግምት በማስገባት ነው፡፡ በዚህ አካሄድ በከተማዋ ዙሪያ የሚኖሩ አርሶ አደሮች ከከተማዋ ዕድገት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የተቀናጀ አሠራር እንደሚዘረጋ ገልጧል፡፡ ያም ሆኖ ሕገ መንግሥቱ አዲስ አበባ ላይ ለኦሮሚያ ክልል የሰጠውን "ልዩ ጥቅም" እንደማይቀበል ፓርቲው በግልጽ አቋም ይዟል፡፡ ኢዜማ ሥልጣን ሲይዝ፣ ሕገ መንግሥቱን በማሻሻል ሂደት ይህን "የልዩ ጥቅም" አንቀጽ አንደሚያስወጣው ነው የሚናገረው፡፡

አብን እንደ እናት ፓርቲ ሁሉ አዲስ አበባ ከተማን በተመለከተ ስር ነቀል የአስተዳደራዊ መዋቅር አማራጭ ያቀረበ ፓርቲ ነው፡፡ አብን ለአዲስ አበባ ይዞላት የመጣው አስተዳደራዊ አወቃቀር ከተማዋ የከተማ ራስ ገዝ ክልል (City State) መሆን አለባት የሚል ነው፡፡ ፓርቲው ለዚህ አወቃቀር ያቀረባቸው ምክንያቶች፣ ከተማዋ የፌደራል መንግሥቱ እና የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ መሆኗን፣ ጅኦግራፊያዊ አቀማመጧን፣ የሕዝብ ስብጥሯን እና ከተማዋ የምትጫወተውን አገራዊ እና ዐለማቀፋዊ ሚና ነው፡፡ ከተማዋ የፌደራሉ መንግሥት መቀመጫ ሆና መቀጠሏን የሚደግፈው አብን፣ ከክልሎች ጋር የሚስተካከል መንግሥት እንዲኖራት እና በፌደራሉ ፓርላማ ተገቢውን ውክልና እንድታገኝ እንደሚያደርግ ይገልጣል፡፡ ከተማዋ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተማ መሆኗን በመጥቀስ፣ ሕገ መንግሥቱ ለኦሮሚያ ክልል የሰጠውን "ልዩ ጥቅም" አብን አይቀበልም፤ አንቀጹም በሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ እንዲወጣ እንደሚያደርግ አቋሙን አሳውቋል፡፡ አብን እንደ ነእፓ ሁሉ ሀገሪቱ ሌላ ተጨማሪ ዋና ከተማ እንዲኖራት ይፈልጋል፤ ለዚህም ዕጩ አድርጎ ያቀረበው እንደ አዲስ አበባ ተጠሪነቷ ለፌደራሉ መንግሥት የሆነችውን እና የአማራ ሕዝብ በአስተዳደሯ አልተወከለባትም የሚላትን ድሬዳዋ ከተማን ነው፡፡

ብልጽግና ፓርቲ ለአዲስ አበባ ከተማ ከእስካሁኑ የተለየ የያዘው አዲስ አቋም የለም፡፡ ፓርቲው በከተማዋ ባለቤትነት እና አስተዳደራዊ ዕጣ ፋንታ ላይ ከቀድሞው ኢሕአዴግ የተለየ አቋም ሳይዝ ነው ወደ ምርጫ የቀረበው ማለት ይቻላል፡፡ ፓርቲው አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ዋና ከተማ ናት ብሎ እንደሚያምን በፕሮግራሙ ላይ አስፍሯል፡፡ አስተዳደራዊ አወቃቀሯን በሚመለከት ደሞ፣ የፓርቲው አቋም ከተማዋ እንደ እስካሁን ቀደሙ ተጠሪነቷ ለፌደራል መንግሥቱ ሆና እንዲቀጥል ማድረግ ነው፡፡ ባንጻሩ ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲዎች በተቃራኒ ከተማዋ ላይ ለኦሮሚያ ክልል የተሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ "ልዩ ጥቅም" አስከብሮ መቀጠል የሚፈልግ ፓርቲ ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ብልጽግና ፓርቲ በአዲስ አበባ ባለቤትነት እና አስተዳደራዊ ውዝግቦች ላይ ወጥ እና ዘላቂ የሆነ አቋም አለው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም ከተማዋ በኦሮሚያ ክልል እምብርት ውስጥ መገኘቷን እና በታሪክም የኦሮሞ ሕዝብ ከተማ እንደነበረች በመጥቀስ፣ የከተማዋ ባለቤት የኦሮሞ ሕዝብ እና ኦሮሚያ ክልለ ነው የሚል አቋም ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች በፓርቲው ውስጥ አሉ፡፡ ይህ አቋም ተደጋግሞ የሚሰማው ደሞ ከኦሮሚያ ክልል የብልጽግና ቅርንጫፍ ፓርቲ ነው፡፡ ፓርቲው እነዚህን ውስጣዊ ቅራኔዎች እንደምን ሊያስታርቃቸው ይችላል? የሚለው ጉዳይ ወዲፊት የሚታይ ይሆናል፡፡

**ማጠቃለያ**

ባጠቃላይ ፓርቲዎቹ በፕሮግራሞቻቸው በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ተመሳስሎሽ እና ልዩነቶች እንዳሏቸው መታዘብ ይቻላል፡፡ በፓርቲዎቹ መካከል በአብዛኛው ተመሳስሎሽ የሚስተዋለው በኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ በውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እና በጥቅሉ በሕገ መንግሥት ማሻሻያ አስፈላጊነት ላይ ነው፡፡ በብሄር ፌደራሊዝም ጉዳይ ላይ ብልጽግና፣ አብን እና ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ ባንድ በኩል፣ ኢዜማ እና እናት ፓርቲ ደሞ በሌላ በኩል ተቀራራቢ አቋም አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

የሀገረ መንግሥቱ አወቃቀር ያልተማከለ ወይም ፌደራላዊ እንዲሆን ቢስማሙም፣ ብሄርን መሠረት ያደረገ አወቃቀር ለሀገሪቱ ይበጃታል ወይስ አይበጃትም? በሚለው ነጥብ ላይ ግን ፓርቲዎቹ ልዩነቶች እንዳሏቸው ንጽጽሩ ያሳያል፡፡ ኢዜማ እና እናት ፓርቲ ብሄር ማንነትን መሠረቱ ያደረገው ፌደራላዊ ሥርዓት ለሀገሪቱ ችግሮች ሁሉ መንስዔ አድርገው የሚያዩና ሥርዓቱ ከስረ መሰረቱ እንዲከለስ አቋም የያዙ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ ከብልጽግና ፓርቲ በስተቀር ሌሎቹ ፓርቲዎች የፌደራላዊ ሥርዓቱ አወቃቀር እንደ መልክዓ ምድር፣ የሕዝብ አሠፋፈር፣ ባሕል፣ የጋራ ስነ ልቦና፣ ታሪክ፣ የልማት እና አስተዳደር አመችነት የመሳሰሉ ሌሎች መሠረታዊ መስፈርቶችን በድጋሚ እንዲያካትት ይፈልጋሉ፡፡ ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ፣ አብን እና ብልጽግና ብሄሮች እና ብሄረሰቦች የሀገሪቱ መሠረቶች እንደሆኑ የሚያምኑ ፓርቲዎች በመሆናቸው፣ የብሄረሰቦች ሙብት የፌደራላዊ ሥርዓቱ አወቃቀር ገዥ መርህ መሆኑ እንዲቀር አይፈልጉም፡፡ ከአምስቱ ፓርቲዎች መካከል የተማከለ የሀገረ መንግሥት ቅርጽ የሚፈልግ ፓርቲ የለም፡፡

ፓርቲዎቹ በአዲስ አበባ ከተማ ባለቤትነት እና አስተዳደራዊ ዕጣ ፋንታ ላይም ልዩነቶች እና አንድነቶች አሏቸው፡፡ እናት ፓርቲ እና አብን ከተማዋ ራሷን የቻለች ክልል ወይም የከተማ ራስ ገዝ ትደግ በሚለው አቋማቸው ይቀራረባሉ፡፡ ብልጽግና እና ኢዜማም አሁን ከተመዋ ለፌደራል መንግሥቱ ያላት ተጠሪነት ራስን በራስ ከማስተዳደር ሙብቷ ጋር እንዲቀጥል በመፈለግ ረገድ ተቀራራቢ አቋም ይዘዋል፡፡ በሌላ በኩል አብን እና ነኢፓ ሀገሪቱ ተጨማሪ ዋና ከተማዎች ይቋቋሙላት የሚል ሃሳብ ተመሳሳይ አቋም ይዘው ብቅ ያሉ ፓርቲዎች ሆነዋል፡፡